# ባንዲራችን በሳንዲያጎ !

**በ ቻቻ ማን ያዘዋል**

July 5, 2008 ሳንዲያጎ ካሊፎርኒያ ቅዳሜ ... ሱፍ ልብሴን ግጥም አድርጌ ለብሼ አምሮብኝ ተውቤ የትግራይ ልማት ማህበር (TDA) የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት ዝግጅት አዳራሽ ስገባ ብዙ ሰው አልነበረም፡; በትልቁ ስክሪን ከዚህ በፊት በተላከ ገንዘብ እየተሰራ ያለውን ት/ቤት ህፃናት ሲማሩበት ሳይ ደስ አለኝ፡፡ የ ስድስትና የ ሰባት አመት ህፃናት ልጆች ከአገር ቤት በተኮላተፈ አንደበት " Thank you TDA ካብ ዳስ ናብ ህንፃ" የሚል መፈክር ሲያሰሙ ሳይ ውስጤን ውርር አደረገው፡; የነዚህን ህፃናት እንባ በማበሳቸው ለ ሳንዲያጎዋች እንኳን ደስ ያላችሁ አልኩ በራሴ ግን አፈርኩ መቼ ይሆን እኔም ያቅሜን ያክል እንዲህ አድርጌ አገሬን የምረዳው ብየ አሰብሁ፡፡

ት/ቤቱ ግን መዝጊያ የለውም መስኮትም አልተበጀለትም የሴቶችና የወንዶች ህፃናት ሽንት ቤት በዚያ የሚያልፍ ሰው ከውጭ ሊያየው ይችላል;; የዚህ ምሽት ዝግጅት ታዲያ ይህንን ጅማሮ ከግብ ለማድረስ ኑሯል!! እኔ ምናውቄ ጥግ ይገሬ የምጠጣውን ይገሬ አደይ አብረሀት በነፃ ለዚህ ዝግጅት ብለው ያዘጋጁትን አምባሻ እየገመጥኩ አስተውላለሁ እኔ ቻቻ ማንያዘዋል ታሪክ ሲሰራ እንድመሰክር ተመርጬ ኑሯል፡፡

ፕሮግራሙ ተጀመረ፡፡ ሊቀመንበሩ አቶ ልዑል መሓሪ እየመሩት ወ/ሮ አልማዝ እጅግ በሚመስጥ መልኩ ይህንን ት/ቤት እንድንሰራውና እንድናጠናቅቀው ተማፅነው ሲገቡ ሁሉም በውስጡ ተነክቷል፡፡ ዶ/ር ፍሰሃ አገር ቤት በቅርቡ ሄዶ እያለ ያስተዋለውን ምስክርነት ስጠ ከዚያ በኋላ ያለውን ግን ካሜራ ካልሆነ ፅሁፍ ይገልጸዋል ብዬ አላምንም፡፡ ወጣቱ ባለሱፍ ታዲያ ይህ ነገር አንድ ነገር እናድርግ ብሎ ገና ንግግሩን ሳይጨርስ "እኔ ካሁን በፊት $300.00 ሰጥቼ ነበር አሁን ደግሞ $700.00 እጨምራለሁ" "እኔ $600.00 እጨምራለሁ" "እኔ ካሁን በፊት $1000.00 ሰጥቼ ነበር አሁን ደግሞ $500.00 እጨምራለሁ"... ስድስት ቆነጃጅት ወጣቶች "በመሃላችን 2,100. ዶላር እንሰጣለን" "እኔ ምንም እንኳ በቅርቡ ቢሆንም ስራ ያገኘሁት 100.00 ዶላር እሰጣለሁ"... ያልተጠራ የቁጥር ዓይነት ያልተሰጠ የገንዘብ መጠን አልነበረም፡፡ መድረኩ ተናወጠ፡፡ ሁለት ወጣቶች እኔ 100.00 ዶላር ብሎ አንዱ ሲናገር ሌላኛው እኔ 300.00 ዶላር ብሎ "ማች"ሲያደርገው በሁለቱ ብቻ $2,900.00 ተዋጣ፡፡ ለአገራቸው ልማት ሲፎካከሩ ማየት ያስቀናል፡፡ ሁለቱ የ ሳንዲያጎ ቻፕተር የ "'ቦርድ አባላት ያደረጉት ፉክክር ደግሞ ሌላኛው አስደሳች ገጠመኝ ነበር፡፡ እኔ 500 ዶላር ሲል ኢንጂነር ጌታቸው እኔ 700.00 ዶላር አለ ፍሰሃ፡